ዓለም አቀፍ ሕብረት ለፍትሕ - የኢትዮጵያ ጉዳይ

Global Alliance for Justice – The Ethiopian Cause; www.globalallianceforethiopia.org; info@globalallianceforethiopia.com

4002 Blacksmith Drive, Garland, TX 75044; Phone: (214)703 9022

# ጋዜጣዊ መግለጫ

ዓለም አቀፍ ሕብረት ለፍትሕ - የኢትዮጵያ ጉዳይ በፍትሕ ለሚያምኑ ድርጅቶችና ሰዎች በሙሉ መልካም ምኞቱን እየገለጸ በቫቲካን ድጋፍ በመርዝ ጋዝ ጭምር በመጠቀም ኢትዮጵያ ላይ ስለ ተፈጸመው የፋሺሽት የጦር ወንጀል የሰው እልቂትና እጅግ ከፍ ያለ ውድመት  የካቲት 12-14 ቀኖች 2007 ዓ/ም ወይም በዚያን ሰሞን በየሐገሩና በየከተማው የመታሰቢያ ክብረ በዓል በማዘጋጀት እንዲዘክሩት ግብዣውን በትሕትና ያቀርባል።



እንደሚታወቀው፤ ፋሺሽት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረችበት በ 1928-34 ዘመን አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ከመጨፍጨፋቸው በላይ 2000 ቤተ ክርስቲያኖችና 525000 ቤቶች ወድመዋል። እንዲሁም በሚሊዮን የሚቆጠሩ እንስሳት አልቀዋል። በተለይ፤ በየካቲት 12-14 ቀኖች 1929 ዓ/ም ፋሺሽቶች አዲስ አበባ ከተማ 30000 ኢትዮጵያውያንን እንደ ጨፈጨፉ የታወቀ ነው። ስለዚህ ማሕበራችን በሚያከናውነው ዓለም አቀፍ ዘመቻ (ሀ)ኢጣልያ ተገበውን ካሣ ለኢትዮጵያ እንድትከፍል፤ (ለ)ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ፤ (ሐ)ኢጣልያና ቫቲካን ከኢትዮጵያ የተዘረፉትን ንብረቶች እንዲመልሱ፤ (መ)የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ኢጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ የፈጸሙትን ወንጀል እንድትመዘግብ፤ እና (ሰ)አፊሌ በምትሰኛ የኢጣልያ ከተማ ለጦር ወንጀለኛው ለግራዚያኒ በቅርቡ የተቋቋመው መታሰቢያ እንዲወገድ እየጣረ ነው።

በዚህም ዓመት በየካቲት 12 ሰሞን እንዲከናወን የሚጠበቀው የመታሰቢያ ክብረ በዓል ቀን፤ በጸሎት፤ በጉባኤ/በስብሰባ፤ እና/ወይም በሰላማዊ ሰልፍ እንዲሆን ይጠበቃል። ማሕበሩ፤ በዚያን ጊዜ የሚሰራጭ የአቤቱታ ደብዳቤዎች ያዘጋጃል።

ማሕበሩ ከፍ ካለ ምሥጋና ጋር የሚያስታውሰው፤ ባለፈው ዓመት የካቲት 12 የመታሰቢይ ቀን የተከበረው በ30 ከተሞች ሲሆን እነርሱም አዲስ አበባ፤ ዋሺንግተን ዲ.ሲ.፤ ኒው ዮርክ፤ ዳላስ፤ ሒዩስተን፤ አትላንታ፤ ሚኒያፖሊስ፤ ሲያትል፤ ሎዛንጀለስ፤ ዴንቨር፤ አውሮራ፤ ቺካጎ፤ ቦስተን፤ ታምፓ፤ ላስቬጋስ፤ ማያሚ፤ ኮሎኝ፤ ሙኒክ፤ ስቶክሆልም፤ ሮም፤ ኢየሩሳሌም፤ ቴልአቪቭ አምስተርዳም፤ ዘሔግ፤ ጃሜይካ፤ ሲድኒ፤ ቫንኩቨር፤ ጆሐንስበርግ፤ ዱባይ፤ እና ለንደን ነበሩ። በዚህ ዓመትም በነዚህና በሌሎች ከተሞች በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ክብረ በዓሉ በሞቀ ሁኔታ እንደሚከበር ይታመናል።

ለተጨማሪ መረጃ ከላይ የተጠቀሰውን ድረ-ገጽ መመልከት ይቻላል።

ቸሩ የኢትዮጵያ አምላክ፤ ለሐገራችን የሚያስፈልገውን ፍትሕ እንድናስገኝ ያበርታን።